# እውን የትውልዶች ግጭት አለ ?
# ያ ዘመንስ ወርቃማ ነበር ወይ ?

**ከገረመው ሃይሉ**

**ታህሳስ 25 ቀን 1999ዓ.ም**

"…Then came the "War Born Generation," born from families who either were an inseparable part of the Dergue regime, worked with or were indoctrinated by it. They are the main victims of the dramatic campaign, the imposition of the ideologies and hateful propaganda of the cruel and hated Ethiopian enemy – the Dergue. Apart from being directly responsible for making our country a battlefield among various rebel groups and for the disintegration of Ethiopia's territorial integrity, this is the worst remnant that the Dergue regime left behind: this generation – the War Born Generation – which was molded to think and envision the world in exactly the same way as the former members of the Dergue regime and its cadres, and who are therefore convinced that the regime of Mengistu Hailemariam did nothing wrong to Ethiopia and Ethiopians. Consequently, the ever-growing clashes and tensions between the two generations – the Golden Period Generation and the War Born Generation – continue to be not only a source of daily conflict, but more worryingly are a potential obstacle to the resistance against the tyrannical regime of Meles Zenewi. …. the War Born Generation, together with those who served the regime of Mengistu Hailemarim, who have skillfully and successfully managed to paralyze all of the engagement planned by the Kinijit Diaspora and Kinijit itself. "

The Revitalization of Ethiopia's Most Tragic, Nightmarish and Painful Memories of the 1970s: The Clash of Generations (Part I) **Dr.** Maru Gubena

"To begin with, our current difficulties seem to me to be explained by the "Cold War" these two generations are waging against each other, with devastating and destructive effects to the path of the Ethiopian resistance. .

The problems and the clashes between the Golden Period Generation and the War Born Generation are much deeper and are getting out of hand: we are at a point where the War Born Generation is ready, not only to politically outsmart and socially silence the Golden Period Generation, but, appallingly, is also working day in and day out to physically eliminate all individuals who belong to the Golden Period Generation"

The Revitalization of Ethiopia's Most Tragic, Nightmarish and Painful Memories of the 1970s: The Clash of Generations (Part II) Dr. Maru Gubena

## መግቢያ ቢሆን

**የዚህ ጽሁፍ መነሻ ዶክተር ማሩ ጉበና ኖቬምበር 24እና ዴሴምበር 16 ቀን 2006 በድረ ገጾች ያሰራጬቸው ሁለት ተከታታይ ጽሁፎችና ይህኑ ጽሁፋቸውን ለማብራራት በአሲምባ የውይይት መድረክ የሰጡት ገለጻ ናቸው። የዶክተር ማሩ ሁለት ተከታታይ ጽሁፎች« ዘ ሪቪታላይዜሽን ኦፍ ኢትዮጵያስ ሞስት ትራጂክ ናይትሜሪሽ አንድ ፔይንፋል ሜሞሪስ ኦፍ ዘ 1970ስ ፡ ዘ ክላሽ ኦፍ ጀነሬሽንስ» ወይም በአማርኛችን በግርድፉ« የ1970ቹን የኢትዮጵያን በጣም አሳዛኝ፤ ሰቅጣጭና ዘግናኝ ትውስታን እንደገና ህይወት መዝራት ፡ የትውልዶች ግጭት» የሚል ነው። የዶክተር ማሩ ጽሁፍ ጭብጥ «የወርቃማው ዘመን ትውልድ» ሲሉ በሰየሙት በእርሳቸው ትውልድና «የጦርነት ዘመን ትውልድ» ባሉት በዛሬው ወጣት ትውልድ መሃል አለ በሚሉት የሁለቱ ትውልዶች ግጭት ነው። ዶክተር ማሩ የትወልዶች ግጭት አለ**

የሚለውን ለማስረገጥም የመሰላቸውን ብለዋል። እኔ በዶክተር ማሩ ጽሁፉ ዙሪያ የምስማማባቸውም የማልስማባቸው ነጥቦች አሉኝ ። እናም እንወያይበት ስላሉ ጽሁፋቸውን አንብቤ ዝም ማለት ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም። የኔ ትኩረት በዋናነት የትውልዶች ግጭት በሚለው ላይ ነው። ሃሳቤን ለማስጨበጥም በመጀመሪያ የትውልዶች ግጭት ለሚለው የራሴን ትርጉም እሰጣለሁ። ከዚያም ዶክተር ማሩ አለ የሚሉትን «የትውልዶች ግጭት» የለም ስል እከራከራለሁ። የ«ወርቃማው ትውልድ» ከሳሾችና ወንጃዮች እነማን እንደሆኑም የማውቀውን ያህል አብራራለሁ። ስለ«ወርቃማው ዘመንም» ትንሽ እላለሁ። ከዚያም የትውልዶች ግጭት እንዳይኖር ካለም እንዳይሰፋ ምን መደረግ አለበት በሚለው ዙሪያ ሀሳቤን ሰጥቼ ጽሁፌን እቋጫለሁ።

በመጀመሪያ ዶክተር ማሩ ሃሳባቸውን በዚህ መልክ አቅርበው ለውይይት በመጋበዛቸው፤ ይህን ጽሁፋቸውን መሰረት አድርጎ የአሲምባ የውይይት መድረክ ዶክተር ማሩን ጋብዞ  የበለጠ ማብራሪያ እንዲሰጡና ሃሳባቸውን የበለጠ ግልጽ እንዲያደርጉ መጋበዙ የሚያስመሰግን ነው።

በዶክተር ማሩ ጽሁፍ ክፍል አንድ ላይ አቶ ይነጋል በላቸው የሰጡትና ኖቬምበር 27 በደብተራው ድረ ገጽ ላይ የውጣውን አስተያየትም እንዲሁ አይቻለሁ። በአቶ ይነጋል ሃሳብ ከሞላ ጎደል እስማማለሁ። እንዲሁም ከዶክተር ማሩ ጋርም

1. የደርጉ ስርአት በመላ አገሪቱ ከፍተኛ ጭካኔ፤ ግፍ፤ ፍጅትና ሰቆቃ ያደረሰ መሆኑ፤
2. ደርግና የደርግ የፕሮፓጋንዳ ማሽን በተቃዋሚዎቹ በተለይም በኢሕአፓ ላይ ከፍተኛ የሃሰት ፕሮፓጋንዳ መንዛቱን እና ይህንም አውነት መስሏቸው የተቀበሉ መኖራቸው፤
3. ከወያኔ ስልጣን መያዝ በኋላ ከ«ወርቃማው ዘመን ትውልድ» የግራ ርእዮት አቀንቃኝ በነበረው ክፍል በተለይም በኢሕአፓ ላይ ያነጣጠረ ክስና ውንጀላ ተጠናክሮ መቀጠሉን  ይህን ለመቀልበስም እውንታውን ሳይታክቱ ማሳወቅ በማስፈልጉ፤

ላይ እስማማለሁ

ይሁንና ዶክተር ማሩ አለ ባሉት «የትውልዶች ግጭት» እና ይህን የትውልዶች ግጭት ለማስረገጥ ባነሷቸው አንዳዳንድ ነጥቦች ላይ እና ከሁሉም በላይ «የጦርነት ዘመን ትውልድ» «የወርቃማውን ዘመን ትውልድን» ሊያጠፋው ሴት ተቀን እየሰራ ነው ያሉት ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አሳማኝ ምክንያት አለማቅረባቸውን እንዲያውም ትክክለኛ ያልሆነ ድምዳሜ መሆኑን ለማሳየት እሞክራለሁ።

## ፩. የትውልዶች ግጭት ምን ማለት ነው?

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ «የትውልዶች ግጭት» ስል በእንግሊዝኛው <ክላሽ ኦፍ ጄኔሬሽን> የሚለውን ሃረግ በአማርኛ ይወክልልኛል በሚል ነው።

የትውልድ ግጭት ተፈጠረ  የተወሰነ የእድሜ ክልል የህብረተሰብ ክፍል ሌላ የተወሰነ የእድሜ ክልል የህብረተሰብ ክፍልን በህብረተሰቡ ውስጥ ለሚታዩት ፖለቲካዊ ወይም ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ወይም ለሶስቱም ችግሮችና ቀውሶች ተጠያቂ የማድረግ ዝንባሌ ነው። በዝንባሌም ብቻ አይቆምም ይህን የትውልድ ክፍል ለመነጠልና ለማግለል መሞከር ነው። በሌላ አነጋገር ይህ የትውልዶች ግጭት ማህበራዊ ቦታ ለማግኘት በሚደረግ ግብግብ የሚፈጠር ነው ሊባልም ይችላል። ይህን ወደ ራሳችን  ሁኔታ በምሳሌ ብናገዘፈው « የጦርነት ዘመን ትውልድ» «የወርቃማውን ዘመን ትውልድን» አሁን ላለው የአገሪቱ ሁኔታ ተጠያቂ ያደርጋል። ይከሳል። ወይም በተገላቢጦሽ  የዶክተር ማሩን አባባል ብዋስ « የጦርነት ዘመን ትውልድ አሁን ላለው ጸረ ወያኔ ትግል ከፍተኛ እንቅፋት ሆኗል» እንዳሉት ማለት ነው።

## ፪. በኢትዮጵያችን የትውልዶች ግጭት  አለ?

ዶክተር ማሩ በጽሁፋቸው እ.አ.አ ከ1938(1930ዓ.ም) እስከ እ.አ.አ1966(1958ዓ.ም) የተወለደውን የወርቃማው ዘመን ትውልድ ሲሉት እ.አ.አ ከ1967(1959ዓ.ም) እስከ እ.አ.አ 1986(1978ዓ.ም) የተወለደውን ደግሞ «የጦርነት ዘመን ትውልድ» ይሉታል። የዶክተሩ ጽሁፍ ማጠንጠኛም «የጦርነቱ ዘመን ትውልድ የወርቃማው ዘመን ትውልድ» ጋር ከፍተኛ ግጭት ውስጥ ገብቷል የሚል ነው። ይህ «የጦርነት ዘመን ትውልድ »የለውጥ ማእከል የነበረውንና የግራ ርእዮት የተከተለውንና ከፍተኛ

መስዋእትነት የከፈለው ትውልድ( የወርቃማው ዘመን ትውልድ) ጋር ቀዝቅዝዛ ጦርነት ውስጥ ገብቷል ይላሉ። የደርግን ፋሺስታዊ ስራዎች በመካድ ደርግን የታገለው ኢሕአፓ ላይ ያነጣጠረ ሰፊ ዘመቻ መከፈቱን በሰፊው ያብራራል። ለዚህ እንደ አስረጅ አድርገው የሚያቀርቡት ደግሞ አሁን ከአገር ውጭ ባለው የቅንጅት አመራር ዙሪያ የተፈጠረውን ቀውስነው።

አንደኛ እንደኔ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያችን ውስጥ የትውልዶች ግጭት የለም። ይልቅስ ገጠና ፈጠ ያለው በተቃዋሚው ጎራ አሁን አገሪቱ ላለችበት የተወሳሰበ ሁኔታ መንስኤና መፍትሄ ላይ የተቀራረበ አመለካከት አለመኖር ነው። ይህ የአመለካከት ልዩነት ደግሞ አሁን በኢትዮጵያችን አራት ትውልዶች አሉ ብንል በነዚህ አራት ትውልዶች አባላት መሃከል ሁሉ የሚንጸባረቅ ነው። ለምሳሌ ኢህአፓን የወለደው የተማሪዎች እንቅስቃሴን የሚከሱና የሚወነጅሉ እንዲሁም ለአገሪቱ ምስቅልቅል ሁኔታ ተጠያቂ ለማድረግ ከሚከጅሉት ውስጥ ከ« ወርቃማው ዘመን ትውልድ » የሚቀድመው ትውልድ አባላት፤ የራሱ የ«ወርቃማው ትውልድ ዘመን» አባላትና «የጦርነት ዘመን ትወልድ» አባላት ይገኙበታል። ሁለተኛ « የወርቃማው ዘመን ትወልድ» ወይም በአቶ ክፍሉ ታደሰ መጽሀፍ መሰረት «ያ ትውልድ» አቶ ይነጋልም እንዳሉት በኢሕአፓ ስር ተሰልፎ የታገለው ብቻ ሳይሆን ከደርግ ጋር ወግነው በነበሩ ድርጅቶች ማለትም በመኢሶን፤ በወዝሊግን፤ በኢጭአት፤ ወዘተ ስር ተሰልፈው ከነበሩት በተጨማሪ ወያኔና፤ ሻቢያን የተቀላቀሉትን «የወርቃማው ዘመን ትወልድ» አባላትን ሁሉ የሚጠቀልል ነው። እናም «የወርቃማው ዘመን ትውልድ» ስንል የወያኔውን ቁንጮ መለስ ዜናዊ ፤ የሻቢያውን ኢሳይያስ አፈወርቂን፤ የኢጭአቱን አሰፋ ጫቦን የወዝሊጉን ሰናይ ልኬን፤ የመኢሶኑን ሃይሌ ፊዳን፤ የኢሕአፓውን አንጃ መሪ ብርሃነ መስቀል ረዳን እና ሌሎችንም እናገኛለን። ይሁንና የዶክርተር ማሩ ጽሁፍ «የወርቃማው ዘመን ትውልድ» በኢሕአፓ ስር ተሰልፈው የታገሉን ብቻ የሚያቅፍ አስመስሎታል።

በሁለተኛ ደረጃ ከላይ እንደገለጽሁት ላሁኑ ችግራችን የ60ቹንና የ70ቹን የተማሪዎች እንቅስቃሴን ተጠያቂ የሚያደርጉ ጥቂት « የጦርነት ዘመን ትውልድ አባላት»ቢኖሩም አሁንም በኢሕአፓ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ አመለካከት ያላቸውና ከቻሉም ከፖለቲካው አለም ገፍትረው ለማውጣት የሚታገሉት በአብዛኛው የደርግን ስርአት ያገለገሉና ምናልባትም ፖለቲካዊ ቁርሾ ያላቸው «የወርቃማው ዘመን ትውልድ» አባላት ናቸው። ብዙዎች በውጭ አገር የሚገኙ የዚያ ትውልድን በተለይም ኢሕአፓን ተችዎችና ከሳሾች እንዲያውም ኢሕአፓን ከደርግና ከወያኔ የበለጠ ተጠያቂ ነው የሚሉትን ብንቃኝ በቁጥር አንድ ደረጃ የምናገኘው የተቃዋሚ ካባ ያጠለቁ ወያኔዎችን ነው። በመለስተኛ ደረጃ ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት ከኢሕአፓ የተለዩ የዚያ ትውልድ አባላት፤ አገሪቱ በአብዮተኞች ብምትናጥበት ወቅት በአድርባይነት ተሰልፈው ከዚህም ከዚያ ሲዋዥቁ የነበሩና ይህ ነው የሚባል ተሳትፎ ያላደረጉ እና ያዩትን እንዳላዩ ሆነው አንገታቸውን ደፍተው ከመአቱና ከግርግሩ ያመለጡ ይገኙባቸዋል። ሌላው «የወርቃማውን ዘመን ትውልድን» በተለይም የ60ዎቹን የኢትዮጵያ ተማሪዎችን እንቅስቃሴዎች የሚተቹት የዚህ ትውልድ አባላት ቁጥር ከዚህ ግባ የሚባል አይደለም ። አብዛኞቹ « የጦርነት ዘመን ትውልድ» አባላት ይህን ክስና ውንጀላ የሚጀምሩት ስደት ከወጡ በኋላና የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ፖለቲካ ከገባቸው በኋላ ነው። ይህ በአንድ ወቅት ፕሮፌሰር መስፍን አሜሪካ ደርሰው ወደ አገር ሲመለሱ « እባካችሁ የውጭው ፖለቲካ እንዳይጋባባችሁ» አሉ የተባለውን ያስታውሰኛል።

እኔ እስከማውቀው ድረስ ከ1980ቹ መጀመሪያ ጀምሮ ደርግ ከመውደቁ በፊትም ሆነ ከወደቀ በኋላ በዩኒቨርስቲ አካባቢ የተደረጉ የተማሪዎችን እንቅስቃሴዎች በቅርበት ብንቃኝ ዶክተር ማሩ የሚሉት ጸረ ኢሕአፓም ሆነ ጸረ «የወርቃማው ዘመን ትወልድ» አቋምም ሲያራምዱ አልታየም ። ይልቁንስ ወያኔ ወደ ስልጣን በተቃረበበትና ስልጣን ከያዘ በኋላ ኢሕአፓን ለመቀላቀል ይፈልግ የነበረውን የዩኒቨርስቲ ተማሪ የሚያውቁ ያስረዳሉ። በመሆኑም «የጦርነት ዘመን ትውልድን» በጅምላ ደርግ ደጋፊና በደርግ መወደቅ ጥቅሙ የተነካ አድርጎ ማቅረብ ማንም የሚቀበለው አይደለም። የደርግ ስርአት በመላው ህብረተሰብ የተጠላ ነበር። ከህብረተሰቡ የነቃውና ከፍተኛ በደል የተፈጸመበት ወጣቱ ትውልድ ደግሞ ጥላቻው ወሰን አልነበረውም። ጠሩ እንዳይፈታ ሞራል ለመስጠት ብላቴ ወታደራዊ ማሰልጠኛ የገባው

ከ9ሸህ በላይ የከፍተኛ ተቋማት ተማሪም ደርግን ወያኔና ሻቢያን  አወገዘ እንጅ አንድም ቀን ተሳስቶ ኢሕአፓን ያወገዘበት ቀን አልነበረም።

ከላይ ለማሳየት የሞከርሁት እንግዲህ በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያ ላይ በእንግሊዝኛው እንዳለ ያስቀመጥኋቸው የዶክተር ማሩ ድምዳሜ ጋር በጭራሽ አለመስማማቴን ነው።

በሶስተኛ ደረጃ ወጣቱ ትውልድ ወይም« የጦርነት ዘመኑ ትውልድ» አሁን በመንቀሳቀስ ላይ ባሉት ፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ኢሕአፓን ጨምሮ እየተሳተፈ ነው። ከፍተኛ መስዋእትነትም ከፍሏል። እየከፈለም ነው። እስከወዲያኛውም ህይወታቸውን አሳልፈውም የሰጡም አሉ።  «የጦርነት ዘመን ትውልድ» አባላት ወያኔን ለመጣል በሚደረገው ትግል ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ በመሳተፍ የድርሻቸውን ለመወጣት ሞክረዋል። ይሁንና እናውቃለን የሚሉ በተለይም ምሁራኖች ደግሞ ጥላቻቸውንና ቅም በቀላቸውን ሊያወርሱት ሞክረዋል። ዶክተር ማሩ ከሚሉት በተቃራኒ «የጦርነት ዘመን ትውልድ» አባላት ታላላቆቹና ይመሩኛል፤ ያታግሉኛል ያላቸው ሲከፋፈሉ፤ ሲወነጃጀሉ፤ እርስበርስ ተጠላልፈው ሲወድቁ በማየቱ ተስፋ ቢቆርጥባቸው ስህተቱ ከታላላቆቹ ነው።  በዚህም የተነሳ ይህንም ያንም ቢተች አይፈረድበትም። ተቸ ማለቴ ግን ለማጥፋት ተነስቷል ማለት አለመሆኑም ግልጽ ነው። ወጣት ነውና በትናንት አሰራሮች ፤ አካሄዶች፤ ዘመን የሻራቸው ገቹና ግልጽነት የሌላቸውን አሰራሮች ቢቃወም ሊፈረድበት አይገባም ሊመሰገን እንጂ። ይልቅስ የፖለቲካ ፓርቲዎች ነባር ሆኑ አዲስ አሳታፊና የወጣቱን ራእይ የሚጋራ አሰራር እስካልቀየሱ ድረስ እየራቃቸው እንደሚሄድ መገንዘብ ይጠበቅባቸዋል። የተቃዋሚው ጎራ ያለበት ሁኔታ እንኳን ወጣት ሞያተኛ ፖለቲከኛ ነን ከሚሉት ጀምሮ ዶክተር ፕሮፌሴሩን ሁሉ ግራ ያጋባ ትርምስ በመሆኑ መፍረድ ይከብዳል።

ከዚህ በመለስ ግን ዶክተር ማሩ ያነሱትና የምስማማበት ጸረ ያ ትውልድ በተለይም ጸረ ኢሕአፓ ፕሮፓጋንዳ በሰፊው መቀጠሉ ነው። የደርጉ ቁንጮ የነበሩት መንግስቱ ሃይለማሪያም አሁንም አይናቸውን ጨፍነው በውሸት ፕሮፓጋንዳችው  በመቀጠላቸው የሳቸው ተከታዮች ከነበሩት በዚያ መቀጠላቸው የሚጠበቅ ነው። ኮሎኔል መንግስቱና የተውሰኑ ኢሕአፓን ወይም ደርግን የታገሉትን ለደረሰው ጥፋት ተጠያቂ የሚያደርጉትና «ቢያስ በሁላችንም በኩል ስህተት ነበር» ለማለት የማይደፍሩት  መደበቅ የሚፈልጉት ወንጀል ያለባቸው ናቸው። ለዚህ ራሳቸውን መንግስቱ ሃይለማሪያምን በምሳሌ አቀርባለሁ። እንኳን ሰው ትንኝ አልገደልሁም ያሉት መንግስቱ ሀለማሪያም እሳቸውና ጓዶቻቸው በአገሪቱ ላይ ለፈጸሙት ጥፋት በተለይም ግልጽ በሆኑት ላይ ሃላፊነትን ውስደው ፖለቲካዊ እርቅ እንዲወርድ የበኩላቸውን ከመጣር ይልቅ አሁን ድረስ እንዴት ሽምጥጥ አድርገው እንደሚክዱና ተከታዮቻቸው የነበሩትንም እስካሁን ድረስ በዚያው በክህደት እንዲቀጥሉ እንዴት እንደሚገፉፉ  ከገነት አየለ የመንግቱ ትዝታዎች መጽሀፍ ሶስት አስረጅ  ጠቅሼ ለማሳየት ልሞክር። በተመሳሳይ ጊዜ (በ1971ዓ.ም.)በደርግ እጅ የወደቁትን ከዚያ ትውልድ ዝነኛ መሪዎች ዋነኛ የነበሩትን የሃይሌ ፊዳንና የብርሀነ መስቀል ረዳን ደርግ አልገደለም ማለታቸው ተጠቃሽ ነው። ኮለኔል መንግስቱ  የመኢሶኑን መሪ ዶ/ር ሃይሌ ፊዳን ደርግ አለመግደሉን ቢክዱም(ገጽ፡ 207፤208፤209) ዶ/ር ሃይሌ ፊዳ ማእከላዊ ምርመራ የሰጡት የምርመራ ቃል ተገኝቶ በመጽሄት  አንበናል። እንዲሁም መንግስቱ ሃይለማሪያም ከኢሕአፓ መስራቾች አንዱ የነበሩትና በደርግ በተመሳሳይ ጊዜ የተረሸኑትን ብርሃነ መስቀል ረዳን የወሎ ገበሬዎች ገደሉት ሲሉ ተፈጽመዋል።  እውነቱ ግን ብርሃነ መስቀል ረዳ በ1971 መጨረሻ አካባቢ ደርግ ጽህፈት ቤት ውስጥ እንደነበሩ ይህ ጸሃፊ ያውቃል። የብርሃነ መስቀል ባለቤት ወይዘሮ ታደለችም የተረፉት የደረሱ ነፍሰ ጡር ስለነበሩ ብቻ ነበር። መንግስቱና መካሪዎቹ ብርሃነ መስቀል ረዳንና ሀይሌ ፊዳን እንዲገደሉ በቂ ምክንያት ነበራቸው። ሁለቱም በውቅቱ ታዋቂና ገናና አብዮተኞች በመንግስቱ ካድሬዎች ዙሪያ በየበኩላልቸው የተውሰነ ድጋፍ ስለነበራቸው መንግስቱ ሃይለማሪያም« ከጀርባቸው ሴራ እንዳይጎነጉኑባቸው» ተስፋ ለማስቀረጥ የነበራቸው አማራጭ እነዚህን የተማሪው እንቅስቃሴ ገናና መሪዎች መረሸን ብቻ ነበር። ሁለቱም ደግሞ አጋጣሚ ጋገኙ ይህን ከማድረግ የሚመለሱ አልነበሩም። ከብርሃነ መስቀል ጋርም ደርግ ምርመር ጽህፈት ቤት ይሰሩ የነበሩ መርማሪዎች ተረሽነዋል የሚባለው ከዚሁ ጋር ሳይሆን አይቀርም። ብዙዎች የኢሕአፓን መዋቅር በማስመታት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱት የብርሀነ መስቀል

ደጋፊዎች በደርግ ጽህፈት ቤትና በከፍተኞች እንዲሁም በመንግስቱ የግል ድርጅት በነበረው አብዮታዊ ሰደድ በተባለው ድርጅት ውስጥ በርካታ ነበሩና ብርሀነ መስቀል ሊድን የሚችልበትን መንገድ ቢፈልጉ የሚጠበቅ ነበር። ሀይሌ ፊዳም መኢሶን ከደርግ ጋር በሰራባቸው ጊዚያት የደርግን ጓዳ ጎድጓዳ የሚያውቅ በመሆኑ በእስራት ብዙ ከቆየ ለመንግስቱ የራስ ምታት ነበር። እናም መንግሥቱ ሃይለማሪያም ሁለቱንም በመረሸን ከጀርባቸው ሊያሴሩ ይችላሉ ብለው ያሰቧቸውን ሁሉ ተስፋ ማቆረጥ ነበረባቸው። መንግስቱ ሀይለማሪያም ይህን ሰይጣናዊ ስራቸውን ለመደበቅ ያላቸው አማራጭ በፍጹም በእጃችን አልገቡም ብሎ መካድ ብቻ ነው። ለነገሩ መንግስቱ ከሲ አይ ኤ ጋር ተደራድረው ከአገር ከወጡ በኋላ «አታለውኝ ነው» ሲሉ መካዳቸውም የሌላ ሳይሆን «አንድ ሰውና አንድ ጥይት እስኪቀር » እታገላለሁ ሲሉ አስራ ሰባት አመት የፎከሩት ስለሚያሳፍራቸው ብቻ ነው። ኮለኔል መንግስቱ ሃይለማሪያም ስለ አስፈጃቸው የኢሕአፓ አባላት ተጠይቀው ሲመልሱም «እንኳንስ የሞቱት ሞላ የኢሕአፓ አባላት 5ሺህ አይሞሉም» ያሉትና« ከሁለቱም ጎራ የሞተው ሁሉ ቢደመር ሁለት ሺህ ይሞላል ብየ አላስብም» (ገጽ፡ 198)፤ ለደረሰው እልቂትም «ተጠያቂው ኢሕአፓ ነው»ያሉትም እንዲሁ ለፈጸሙት ተወዳዳሪ ለሌለው አረመኔዊ ድርጊታቸውን የሚያቀልላቸው ስለሚመስላቸው ነው። እናም የተወሰኑ የደርግ ስርዓት ካድሬዎች መንግስቱ የሚክዱትን ቢክዱ የሚጠበቅ ነው።

ትልቁ ችግር ያለው ግን በትምህርት የገፉትና እንዲሁም የእድሜውና የልምድ ባለሞያዎች ከቂም በቀል፤ ከስሜት፤ ከጥላቻና ከግትርነት ርቀው ሃቁንና እውነቱ ለወጣቱ ለማሳወቅ አለመትጋታቸው ነው። በዚህም የተነሳ እውነትና ውሸቱን ለመለየት እስከሚቸግር ድረስ ለደረሰው ውዥንበር ተባባሪ መሆናቸው ነው።

## ፫ኛ. ወርቃማ ዘመንስ ነበርን ?

በመጨረሻም በዶክተር ማሩ ጽሁፍ የማልስማማበት ወርቃማ ባሉት ዘመን ነው። ዶክተር ማሩ በአሲምባ የውይይት መድረክ ወርቃማ ያሉት ትውልዱን ሳይሆን ዘመኑን መሆኑን አብራርተዋል። እንደ ዶክተር ማሩ «የወርቃማው ዘመን ትውልድ» የትውልድ ዘመን ከ1930 እስከ 1958 ዓ.ም ነው። ይህ ከሆነ ዘንዳ ከ1928 እስከ 1933 በጣሊያን ተወራ የነበረችበትንና ጣሊያንን በእንግሊዞች እርዳታ ካባረርን በኋላም እንግሊዞች ለእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አገሪቷን በደንብ ያመቻቹበትን ዘመን ወርቃማ ለማለት ይከብደኛል። ያ ዘመን ከኢትዮጵያ ህዝብ ቢያንስ ከ75 እስከ 80 በመቶ እጅ በላይ የሚሆነው በገጠር የሚኖር ነበር። በደቡብ ኢትዮጵያ በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠር ህዝብ በጭሰኝነት የሚማቅበት፤ በስሜን ረሃብ በተደጋጋሚ ህዝቡን የሚያቀራምደበት፤ በመሬት ይገባኛል ክርክርና ሙግት ገበሬው ለይግባኝና ለሙግት ያለችውን ሻሽጠ በአመታት የፍርድ ሄደት የሚንገላታበት ዘመን ቢያንስ ለገበሬው ወርቃማ አልነበረም። ሰው ይሽጥ ይለወጥ የነበረበን ዘመንም ወርቃማ ዘመን ማለት አይቻልም። ከሁሉም በላይ ተምሮ አገሩን ሊያሳድግና የህዝቡን ኑሮ እንዲለውጥ ተስፋ የተጣለበት ወጣት ትውልድን ለአውሮጳ አሜሪካ አገልጋይነትና አገሪቱን ለጥገኝነት የቀረጸን ስርአተ ትምህርትንም ቢያንስ ዛሬን ሆነን ልንኮራበት የሚገባ ሆኖም አላገኘሁትም። የነበረው የሃይማኖት ጭቆናም ቢያንስ በሙስሊሙ ህብረተሰባችን ዘንድ ዘመኑን ውርቃማ አያሰኘውም። የብሄረሰቦች ጭቆናውም እንዲሁ ዛሬ የባሰ አገር አተራማሽ ሁኔታ ስለመጣ ልንረሳው የምንችልና ሁሉም የሚኮራበት ወርቃማ ዘመን ነበረን ሊባል የሚያስደፍር ሆኖ አላገኘሁትም። ይልቁንስ ያ ዘመን ኢትዮጵያ አሁን ወዳለችበት ሁኔታ የሚያንደረድሩ ሁኔታዎች በገሃድም ውስጡ ውስጡንም ይብላሉ የነበረበት በመሆኑ ወርቃማ ልለው ይከብደኛል። እና በዚህም እለያለሁ። ያ ትውልድም የታገለው ይህ ከላይ ብትንሹም ቢሆን የጠቃቀስኳቸው ችግሮች ለማስወገድና ልማትና ብልጽግናን ለአገሩ ተመኝቶ ነበር። እናም ያን ዘመን ወርቃማ ዘመን ማለት የዚያኔ ተማሪን ጨኸት «የጥጋብ ነው» ያሰኛል።

ዶክተር ማሩ «የወርቃማው ዘመን ትውልድ» ተማሪን ከ«ጦርነት ዘመን ትውልድ» ተማሪ ጋር አወዳድርው ያሁኑ ዩኒቨርስቲ የጨረሰ እንኳ በእንግሊዝኛ ማመልከቻ መጻፍ አይችልም ሲሉ የተቹትም አግባብ ያለው ሆኖ አላገኘሁትም። በመሰረቱ ከዛሬ ሀምሳ አመታት በፊት የነበረ የኢትዮጵያ ሁኔታ በእጅጉን የተለየ ለመሆኑ ግልጽ ነው። ያኔ በከፍተኛ እንክብካቤ በአገርም ሆነ በውጭ አገር ምርጥ አስተማሪዎች አማካይነት ለአገሩ ሳይሆን ለአውሮጳውያን አገልጋይ እንዲሆን በተቀረጸ የትምህርት ፖሊሲ የተማረውን የዚያኔን ተማሪና በአንድ ክፍል ከ60 እስከ 100 እየታጨቀ በሰቀቀንና በትርምስ ውስጥ

የተማረን የዘመነ ወያኔና የዘመነ ደርግ ተማሪን ማወዳደር የሚ.ታሰብ አይመስለኝም። ዶክተር ማሩ ይህን ወጣት ትውልድ ያገሩን ቋንቋና ታሪክ የማያውቅ ሆኖ ቢያገኙትና ቢ.ተቹት እደግፋቸው ነበር።

## <u>የትውልዶች ግጭት እንዳይነሳ ካለም እንዳይሰፋ ብሎም እንዲጠብ ምን ማድረግ ያስፈልጋል ?</u>

የትውልዶች ግጭት የለም ብያለሁ ከላይ። አለ ከተባለ ደግሞ ልዩነቱን በማራገብ ሳይሆን እንደኔ የመጀመሪያው እርምጃ ቅን አስቦና የአገሩን እድገት ተመኝቶ ለለዴሞክራሲ.ያዊ ስርአት ግንባታና ለለውጥ የታገለውን የለውጥ አንቀሳቃሽ ትውልድ ታሪክ ፤ደካማና ጠንካራ ጎን ትምህርት በሚሰጥ መልኩ አዘጋጅቶ እውነታውን ሳይሰለቹ በማሳወቅ ከስህተቱም ሆነ ከድክመቱ ትምህርት እንዲቀስምበት ማድረግ ነው። የሚበጀውም ይኸው ነው። የትውልዶች ግጭት እንዳይከሰት ሁለተኛውና እጅግ ከፍተኛ ትኩረት ሊ.ደረግበት የሚገባው በየትኛውም አገራዊ ጉዳዮች ላይ ሁሉንም የትውልድ ክፍሎች እና የማህበረሰብ ክፍሎች ማሳተፍ ነው። ይህን ማመቻቸትና ተነሳሽነትን መውሰድ ያለባቸው እንደ ዶክተር ማሩ አይነቶች ከወጣቱ ትውልድ በድሜ፤ በልምድና በትምህርት የገፉት ናቸው። ባሁኑ ወቅት የአገራችን ችግሯ ከፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ ያለፈ መሆኑን መረዳትና ሁሉም አስተዋጽንኦ ማድረግ ያለበት መሆንን መገንዘብ ነው። ለዚ.ህም የአገራችንን ችግር ለመፍታት ሲ.ታቀድ ከፖለቲካ ድርጅቶች በተጨማሪ የአገር ሽማግሌዎች፤ ወጣቶች፤ የሰቪክና የሞያ ማህበራት፤ የተለያዩ ሞያዎች ሊ.ቃውንቶች፤ የሴቶች፤ የሃማኖት አባቶችን ያካተተና ያሳተፈ መሆን አለበት የሚባለውም ለዚ.ህ ነው። ዶክተር ማሩ የጠቀሱት የትውልዶች ግጭት እንዳይነሳ ካለም እንዳይሰፋ አዲሱ ትውልድ በህብረተሰቡ ውስጥ ተገቢውን ቦታ ማግኘት አለበት። ወጣቱን ትውልድ አሜሪካና አውሮጳ ናፋቂ ፤ የጫትና የሌሎች እጾች ሱሰኛ፤ ቦዘኔ፤ በአገሩ ላይ ተምሮና ሰርቶ የመኖር ተስፋው የጨለበት እንዲሆን ያደረገውን የወያኔን ስርአት ለመታገል በሚደረገው ትግል ውስጥ ከላይኛው አመራር ጀምሮ እስከታችኛው እርከን ድረስ በችሎታና ብቃታቸው መሰረት ማሳተፍ ወሳኝ ነው። እኔ አውቅልሃለሁ ጊዜው አልፎበታል። ትግሉ አዲስ በዚ.ህም በዚ.ያም ያልተቀየደ አስተሳሰብ ያላቸው ብሩህ ወጣት« የጠርነት ዘመን ትውልድ አባላትን» ይፈልጋል። ይህ ማለት ግን አሁን አልፎ አልፎ የሚ.ታየውን «ሳይሞቅ ፈላ»ነትን ማበረታታ አይደለም። በወጣቱም ሆነ በሌላው ዘንድ የአስተሳሰብ ለውጥ መኖር እንዳለበት በቅርቡ <u>"Unity of Purpose: changing mindsets to sustain Ethiopia's democratization"</u> በሚል አቶ እውነቱ ፈለቀ ያቀረቡት እጅግ ጠቃሚ ምክርና ጥናታዊ አስተያየት ተጠቃሽ ነው ። ከትምህርትና የእድሜ እንዲሁም የልምድ ባለጸጎች የምንጠብቀውም እንደ አቶ እውነቱ አይነት ያለ ምክርና ልዩነቶቻችን የሚያቻችልና የሚያጠቡ ህሳቦችን ነው።

መልካም ገና

ለክርቲያን ወገኖች ሁሉ